በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የ6ኛ ክፍል 1ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና

ግብረ ገብ, ሰኔ 2016ዓ.ም/ JUNE 2024G.C

የጥያቄ ብዛት: 40 የተፈቀደው ሰዐት: - 1 ሰዐት

**አጠቃላይ ትዕዛዝ**

ይህ የግብረ ገብ ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት። ለምሳሌ የጥያቄው መልስ የተመረጠው "ሐ" ቢሆን ከዚህ በታች ባለው መልኩ መልስ መስጠት አለበት

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ○ | ○ | ● | ○ |

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው። ሰዐት ሲያበቃ የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዐት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ።

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

LIVEWORKSHEETS

**መመሪያ አንድ፥** ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ድረስ የግብረገብ ምሉዕነትን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ

1. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች "ምሉዕነትን" በይበልጥ የሚገልጸው የትኛው ነው?

   ሀ. ሰዎች የሌሎች ሰዎችን መሰረታዊ እምነትና ድርጊት ሲቀበሉና ሲተገብሩ
   
   ለ. ሰዎች ስለ ነገሮች ባላቸው ግላዊ እምነት ቋሚ አመለካከትን ሲያንጸባርቁ
   
   ሐ. ሰዎች የራሳቸውን መሰረታዊ እምነት በሌሎች ሰዎች ላይ መጫን ሲችሉ
   
   መ. ሰዎች ስለነገሮች ባላቸው ግላዊ እምነት ተለዋዋጭ አቋምን ሲየሳዩ

2. ከሚከተሉት አንዱ የምሉዕነት የተላበሱ ግለሰቦች ባህሪ የሆነው የትኛው ነው ?

   ሀ. የሰሩትን ስህተት በእራሳቸው መቀበል ይችላሉ
   
   ለ. ሌሎች የተሳሳተ ድርጊት ሲፈጽሙ በዝምታ ይመለከታሉ
   
   ሐ. የፈጸሟቸውን ድርጊቶች በአጽንኦት መገምገም ይቸገራሉ
   
   መ. ውስጣዊ እምነታቸውን በማይገልጽ ተግባር ላይ ይሳተፋሉ

3. እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሱ ሰዎችን ባህሪ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. በዙሪያቸው ካሉ ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ተገቢውን ዋጋ አይሰጡም
   
   ለ. የሌሎች ሰዎችን ሚስጥሮች ለሌሎች አሳልፈው ይሰጣሉ
   
   ሐ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም እውነትን ይናገራሉ
   
   መ. በሌሎች ላይ ጉዳት የሚያስከትል ነገር ሲመለከቱ አይቃወሙም

4. ከሚከተሉት የግብረ ገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ በራሳቸው የሚተማመኑ ጠንካራ የስራ ባህል ያለው ማህበረሰብ ይፈጥራል
   
   ለ. በቀላሉ የገቡትን ቃል የሚያፈርሱ ግለሰቦች መበራከት
   
   ሐ. ችግሮችን በብቃት የመፍታት አቅምን ያሳጣል
   
   መ. መጥፎ ተግባራትን የሚያጋልጡ ግለሰቦች ማነስ

5. ከሚከተሉት ውስጥ እውነተኛ ግብረገብነት የተላበሰ ሰው ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ግብዝነት
   
   ለ. እውነተኛነት
   
   ሐ. ብርታት
   
   መ. ትህትና

6. ከሚከተሉት አንዱ ማጭበርበርና ስርቆትን በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው ?

   ሀ. ጠንካራ በራስ የመተማመን ችሎታን ያዳብራሉ
   
   ለ. መጥፎ ድርጊትን በድፍረት መቃወም ይችላሉ
   
   ሐ. በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን እምነት አያገኙም
   
   መ. እውነተኛ ወዳጅነትን ለመመስረት ይችላሉ



LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ሁለት፣ ከተራ-ቁጥር 7 እስከ 13 ድረስ የህግ ተገዢነትን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ ምረጪ.

7. የህጎችን ምንነት በተለመከተ እውነት የሆነው የትኛው ነው

ሀ. ከዜጎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት የላቸውም
ለ. ጥቂት ዜጎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነምግባር ደንቦች ናቸው
ሐ. በፍጥነት ተለዋዋጭና ወጥነት የላላቸው መመሪያዎች ናቸው
መ. የዜጎችን መብትና ግዴታ የሚያሳውቁ መመሪያዎች ናቸው

8. ለህግ ተገዢ የሆኑ ዜጎች የቋንቋ፣ ሀይማኖትና የባህል ግጭቶችን በ________________ ይፈታሉ.

ሀ. በጦርነት
ለ. በእድርባይነት
ሐ. በሰላም
መ. በቸልታ

9. የህግ ተገዢነት ጠቀሜታ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሙሉ ነጻነትና እኩልነት ማግኘት
ለ. የሚፈልጉትን ሀይማኖት መከተል አለመቻል
ለ. በፖለቲካ ለመሳተፍ ፈቃድ ማጣት
መ. የራስን የንግድ ስራ ለመስራት መከልከል

10. ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዢ የሆኑ ሰዎች ባህሪ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. መብትና ግዴታን ጠንቅቆ አለማወቅ
ለ. ህግን ከማወቅና ከማክበር መቆጠብ
ሐ. ህግን እንደፈለጉ መጣስ
መ. ህግ ሲጣስ ለሚመለከተው ማሳወቅ

11. ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዢ አለመሆን አሉታዊ ውጤት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የሰላም እጦት
ለ. የዜጎች ፍላጎት መጠበቁ
ሐ. ፍትሃዊ የሀብት ክፍል መኖሩ
መ. የሰብአዊ መብቶች መከበሩ

12. ከሚከተሉት አንዱ ለህግ ተገዢ የመሆን ውጤት ነው

ሀ. ስርአት አልበኝነት
ለ. የሙስና መስፋፋት
ሐ. የመብቶች መጣስ
መ. በነጻነት መኖር

13. ከሚከተሉት ውስጥ ግብርን የሚሰውሩ ሰዎች ባህሪ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ገቢን አሳንሰው አያቀርቡም
ለ. የተጋነነ ወጪን ለማቅረብ ይቆጥባሉ
ሐ. ሀሰተኛ የግብር ሰነድ ማዘጋጀት
መ. ትክክለኛ ግብርን ማሳወቅና መክፈል



LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ስስት፡ ከተራ ቁጥር 14 እስከ 20 ድረስ ጥሩ ስለምግባርን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ ምረጪ

14. ከሚከተሉት የመልካም ስነምግባር የሆነው የትኛውነው?

ሀ. ትህትናን ማጣት

ለ. በራስ አለመተማመን

ሐ. ስህተትን አለመቀበል

መ. ጥሩ ጓደኞችን መምረጥ

15. ከሚከተሉት መልካም ስነምግባር የተላበሰ ሰው ባህሪ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. እራስ ወዳድነት

ለ. ደግነት

ሐ. ማጭበርበር

መ.ፍርሃት

16. የመልካም ባህሪ መገለጫ ክብር መስጠት ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ. ለአካባቢ ክብር መስጠት

ለ. ለራስ ብቻ ክብር መስጠት

ሐ. ለወላጅ ክብር መስጠት

መ. በሀላፊነት ላይ ለተቀመጡ ሰዎች ክብር መስጠት

17. ከሚከተሉት አንዱ የመልካም ስነ ምግባር ባለቤት መሆን ጠቀሜታ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሰዎች ዘንድ አመኔታን ማግኘት

ለ. የመልካም ግንኙነት መጓደል

ሐ. የጓደኛ እጦት

መ. ከሌሎች ሰዎች ጋር መጋጨት

18. አንድ ሰው ሀሳቡን ስሜቱን፣ ፍላጎቱንና ልምዶቹን የመቆጣጠር ብቃት ካለው የትኛውን የመልካም ስነ ምግባር ዘዴ አዳብሯል ማለት ይቻላል?

ሀ. የትምህርት ቤት ህግና ደንብ ማክበር

ለ. የማህበረሰብ እሴትን ማክበር

ሐ. ራስን መቆጣጠር

መ. ለህግ ተገዢነት

19. ከመልካም ስነምግባር ማበልጸጊያ ዘዴዎች ውስጥ የሚካተተው የትኛው ነው?

ሀ. የግበረገብ መርሆዎችን ለመተግበር የሚያስችል ብቃት አለማሳደግ

ለ. ታማኝ መሆንና የገቡትን ቃል መጠበቅ የሚያስችል ብቃትን አለማዳበር

ሐ. አላስፈላጊ የሆኑ ምኞቶችንና ተግባሮችን ማከናወን

መ. ሀላፊነትን መወጣትና ለተጠያቂነት መዘጋጀት



LIVEWORKSHEETS

20. ከሚከተሉት ውስጥ የመልካም ስነ ምግባር አለመላበስ ውጤት የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ. እውነተኛነት
ለ. የእርስ በእርስ ግጭት
ሐ. ታማኝነት
መ. ሚስጢር ጠባቂነት

**መመሪያ አራት፡** ከተራ ቁጥር 21 እስከ 28 ድረስ የማህበራዊ ምጣኔ ጉዳዮች ላይ መሳተፍን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ ምረጪ

21. ከሚከተሉት ውስጥ ማህበራዊ ተሳትፎ ምሳሌ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጫማ መጥረግ
ለ. በጎ ፈቃደኛነት
ሐ. በሱቅ ላይ እቃ መሸጥ
መ. እርሻ ላይ መስማራት

22. ከታች ከተጠቀሱት በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚካተተው የትኛው ነው?

ሀ. የገንዘብ ልውውጥ ማድረግ
ለ. ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት
ሐ. ምርቶችን ማምረትና መሸጥ
መ. ገቢ ማግኘትና ሀብት ማፍራት

23. የበጎ አድራጎት ተግባራት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ.ገንዘብና ሽልማት ተቀብሎ መስራት
ለ. በሙሉ ፈቃደኝነት ማገልገል
ሐ. የአካባቢ ጥበቃ ስራ
መ. ድሀ የማህበረሰብ ክፍልን መርዳት

24. ከሚከተሉት ወስጥ ስለበጎ ፈቃድ ማህበራዊ አገልግሎት እውነት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የማህበረሰብ አኗኗርን ለማሻሻል አስተዋፅኦ የለውም
ለ. አካባቢያዊና ሀገራዊ እድገት አያመጣም
ሐ. የመንፈስ እርካታ ያስገኛል
መ. የግል ትርፍና ጥቅምን ያስገኛል

25. ከሚከተሉት ውስጥ የጋራ ጥቅም ምሳሌ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. መሰረተ ልማት
ለ. የቤት መኪና
ሐ. ንጹህ አካባቢ
መ. ቤተ መጻህፍት

26. ግብርን በታማኝነት የመክፈል ጠቀሜታ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የዜጎች የመሰረተ ልማት ተደራሽነትን ያጓትታል
ለ. የተለያዩ አገልግሎቶች ለመስጠት እንቅፋት ነው
ሐ. የግለሰቦች ገቢ እና ሀብት ያድግበታል
መ. ድህንነትን ለማስወገድ በከፍተኛ ሁኔታ ይረዳል

27. ከሚከተሉት ውስጥ የባህላዊ ቁጠባ ተቋም የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ. ባንክ
ለ. እቁብ
ሐ. አነስተኛ የፍይናንስ ተቋማት
መ. የመድህን ድርጅቶች



LIVEWORKSHEETS

28. ከሚከተሉት ውስጥ የሀገር መውደድን የሚገልጽ የትኛው ነው?

ሀ. ለሀገር ያለ የታማኝነት መንፈስ ማነስ
ለ. የግል ጥቅምን ማስቀደም
ሐ. ለሀገር ጥልቅ ፍቅር ማሳየት
መ.ማህበረሰብን ለማገልገል ፍላጎት ማጣት

**መመሪያ አምስት፡ ከተራ ቁጥር 29 እስከ 34 ድረስ የሀገር ፍቅርን መሻትን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ ምረጪ.**

29. ከሚከተሉት ውስጥ የሀገር ወዳድነት መገለጫ የሆነው

ሀ. የባለቤትነት ስሜት ማጣት
ለ. በሀገር ሉአላዊነት አለመኩራት
ሐ. ሙስናን መፈፀም
መ. ጀግኖችን ማክበር

30. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሀገር ወዳድ የሆኑ ዜጎች መብዛት ለሀገር ከሚሰጠው ጠቀሜታ የሆነው የትኛው ነው

ሀ. የተንሸራሸረ አንድነት መኖር
ለ. ፈጣን እድገት አለመኖር
ሐ. ለሌሎች ጥቃት መጋለጥ
መ. ሀገሩን የሚወድ፡ መሪ መፈጠር

31. ሀገር ወዳድ የሆኑ ግለሰቦች ሚና የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የራስን ፍላጎት ብቻ ማራመድ
ለ. ለሀገር እድገት አነስተኛ አስዋፅኦ ማድረግ
ሐ. የሙስናን ተግባርን ማስወገድ
መ. ስልጣንን ያለአግባቡ መጠቀም

32. ከታች ከቀረቡት ሀገርን መውደድ ውስጥ የሚካተተው የትኛው ነው ?

ሀ. ትውልድ ሀገሩን እንዲያውቅ ማድረግ
ለ. በተግባር የሀገርን ፍቅር ለማሳየት መቸገር
ሐ. ሀገርን ለመጠበቅ ዝግጁ አለመሆን
መ. ከማህበረሰብ ራስን ማራቅ

33. ከሚከተሉት ሰላማዊ ባህሪ ምሳሌ የትኛው ነው?

ሀ. ጥላቻ
ለ. የበታችነት ስሜት
ሐ መከባበር
መ. አለመግባባት

34. የሰላም ጠቀሜታ የሆነው የትኛው ነው ?

ሀ. ችግሮችን በሃይል መፈታት
ለ የተግባቦት ክህሎት መበልፀግ
ሐ. በራስ መተማመን ማጣት
መ. የሁከትና መገለል መስፈን



LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ስድስት፣ ከተራ-ቁጥር 35 እስከ 40 ድረስ ሰላምና ትብብርን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ ምረጪ

35. ከሚከተሉት ውስጥ መተባበርን የሚገልጽ የትኛው ነው?

ሀ. እርስ በእርስ አለመረዳዳት
ለ. አገልግሎቶችን አለማዳረስ
ሐ. የሌሎችን ሀዘንና ደስታ መካፈል
መ. ተራን ሳይጠብቁ መስተናገድ

36. ከሚከተሉት መተባበርን ለማሳደግ የማይጠቅመው የትኛው ነው?

ሀ. የሌሎችን ሚስጥር አሳልፎ መስጠት
ለ. ከሌሎች ጋር መተማመን
ሐ. ምቹና ሰላማዊ የሆነ አካባቢ መፈጠር
መ. እርስ በእርስ መረዳዳት

37. ከሚከተሉት የመተባበር ጠቀሜታ የሆነው የትኛው ነው

ሀ. ከሌሎች ጋር ያለውን ተግባቦት ያዳብራል
ለ. ሌሎችን ለማድመጥና ለመረዳት ያዳግታል
ሐ. በጥልቀት ማሰብን አያጎለብትም
መ. የእራስ ወዳድነት ይንጸባረቅበታል

38. ግልጽነት ምን ማለት ነው

ሀ. ስሜትን መደበቅ
ለ. ሀሳብን በታማኝት መግለጽ
ሐ. ውሸትና ማስመሰል
መ. ሁሉንም ሀሳብ መቀበል

39. የሰላምና ትብብር መኖር ውጤት የሆነው

ሀ. ግጭትና ጦርነት
ለ. የሀገር አንድነት መጠናከር
ሐ. የመንግስታት መውደቅ
መ. የሰዎች ሞትና መፈናቀል

40. ከታች ከቀረቡት ስለሰላምና ትብብር ስህተት የሆነው የትኛው ነው

ሀ. ሰላምና ትብብር የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ናቸው
ለ. ሰላምና ትብብር በጥቂቶች ርብርብ ይገኛሉ
ሐ. ሰላምና ትብብር የሰዎችን ደህንነት ያስከብራሉ
መ. ሰላምና ትብብር በዜጎች ትብብር ይረጋገጣሉ



LIVEWORKSHEETS